## "ንስሃ" ያውቅ ብለህ?

በኮስሞስ-2000, መጋቢት 2010

ገና ስትፈጠር ሳለህ ግልገል
ጎዳናውን ስተህ ገባህ ገደል::
ስጋዊ ግኝትህ ቢሆንም ከአባትህ
እንዲሁም ከአያትህ
የባንዳነቱ መሠረትህ
አባ ዲያቢሎስ ነው የመንፈስህ
መምህሩ የቅኝትህ::

የብፁዕ አባትህ ቃል እንዲህ ይላል
"ገና ስትወለድ ምህረት ተሰጥቶሃል
ገነትንም እንደምትወርስ ፀድቆልሃል
ከመንበረ ፀባዖቱ ፊት ለፊት ቁመሃል
ወርቅ እንደሆንክ አብስሮሃል
ኀጥያትህም ተሰርዟል
ገና በልጅነትህ ትንቢቱ ተነግሮሃል”
ቢሆንም ቅሉ
የሕዝባችን ምሬት የሃዘን ጩኸት
የተሰማ ይመስለኛል ለመዳኘት::

አዲሱ ንጉሣችን ማቅ ለብሰው
ዘመናዊ መሳፍንታቱም ተርመስምሰው
ሁሉም ይታያሉ እንደንጉሡ አጎንብሰው::
የሠራዊቱም ዋና ዋና አዛዦቹ
ባንዳዎቹ ካድሬዎቹ
በድያለሁ ሳይሉ ተንበርክከው
ሳይፀፀቱ እንባቸውን ፍስስ አርገው

ሃዘንተኛውን ሕዝብ        ካልተማፀኑ
ምኑን ንስሃ ገቡ?        ምኑን ጻኑ?
ይህ ካልሆነማ
ሲበታትኩን የነበሩት        ቀበኞች
አይባሉም የእኞች::
"ተለዋጮቹ"
መዳን ካልፈለጉ        ዐምነው
ይጠፋሉ እንደጨው        ሟሙተው
ዕምነት ስላጎደሉ!
መለወጥ ስላልቻሉ!

የሕፃን ሽያጭ        ደርቶ ሲጋለጡ
በአረብ ምድር        ሴቶቻችን ሲዋረዱ
በክህደት ላይ ክህደት        ሲያራምዱ
በግብፅ ምድር        በጥይት እየተገረፉ
ወይ ድፍረት!        ጊዎንን ሊያስገድቡ
በሚስጢር        እየተግባቡ
ብቅ ይላሉ!        እኛን ሊጎበኙ
ቀድመው ሸጠውናል        አትሞኙ::
መውጫ መግቢያውን        በሩን ዘግተው
በእብሪት ተነሳስተው        ጀግና ገድለው
በረሃብተኛው ሬሳ        እየነገዱ እጅግ ከብረው
ማሩን! አጥፍተናል!        እንዴት አይልም ሰው?

በየቀኑ ክህደት        በየቀኑ ወንጀል
ቅኝ መገዛትንማ        ሕዝቡ አይቀበል::
ምድር ቁና ሆና        ብትደናበር
"ወይ ለከይ አደዋ"        ለማለት ዛሬ ብትቸገር

እነሆ ተናዘዛ! ቀልጠፍ በል! አትግደርደር!
ሳትሸፍጥ! አጋልጥ! እራስህን ቁልጭ አርገህ
ምህረት ጠይቅ! ደፈር ብለህ!
መጠየቅ ብቻ ሳይሆን በግብር እያሳየህ
የበደልከውን ክሰህ
በግብር ብቻ ሳይሆን በጥልቅ አምነህ
በፅኑ መለወጥህን አሳይተህ
ያገርህ ሰው እንዲያምንብህ
እንደጥንቱ!
ምልክት አድርግ ከግንባርህ::
አዬ ዮሐንስም አዘዋል እኮ! አይዞህ!
ላንተ አዲስ አይደል! ምን ችግሮህ?
ዕወቅ!
የተለወጠ ሁሉ መሰዋትም እንዳለበት
ለሃገርህ! ለድንበርህ! ለአንድነት!

እንዲያ!
ምሳሌ ሁን! ዕመን እንጂ የገድልከውን
መፍታትማ ፍታ እንጂ ያሠርከውን
ንብረት መልስ የስርቆቱን
የላባቸውን የድሆቹን
መልስላቸው!
እጥፍ ድርብ አርገህ ሃብታቸውን::

ያንተ ዛፍ የተከልከው ከሌላው ልዩነቱ
የመርዝ ፍሬ ማፍራቱ ነው በያይነቱ::
ብዙ ናቸው በልተው የታመሙ በጠዋቱ
ንገረና ምን እንደሆነ መድሃኒቱ?

አልነግርም ካልክ ተወጥረህ በትቢቱ
በመጥረቢያ ተቆራርጦ
ከወደ ሥሩ ተመንግሎ
ይወረወራል ለቃጠሎ
እንዳያጨበጭብ ተመልምሎ::
ስማ በድጋሚ!
“ድህነት” መሰዋትን ይጠይቃል
ካመንክበት ፈጣሪም ተናግሮታል
ቃሉን አንብ
ለማንበብማ አንተን ማን ይበልጣል?

እኔን እኮ የሚያናግረኝ
ፈጣሪዬ ይሆናል እያዘዘኝ
ጊዜውም የቀረበ እየመሰለኝ
ይህቺን ቀን
ሳልተነፍስ እንዳታልፈኝ
ዋ! እምቢ ካልክ አንተን አያድርገኝ::

ቅጥ የለሺ ጦርነት አውጀህ
አገር ወዳጆችን ፈጅተህ
ቅኝ ገዥ ነኝ ብለህ አምነህ
እናት አገርህን አስደፍረህ
ሕፃናትን ወላጅ አልባ አሰቀርተህ
እናቶችን የደም እንባ አስለቅሰህ
ድፍን አገሩን በረሃብ አስጠብሰህ
ከአገር እንድንወጣ እሰድደህ
በቆሻሻ ቱቦ ልጆችን አሳድረህ
በጥቅሉ አገር ገድለህ

እኮ! ለምን እንጂ ተንበርክከህ!
ስለ እግዚአብሔር ማሩኝ! ብለህ!

አይመጣብን የለ ዘንድሮ
ሰላሳው ዓይነት በውጭ ተደርድሮ
ዘጠና ድርጅት ባገሬ ውስጥ ተዋቅሮ
ተንዛዝቶበት ግፈኛው ተደናግሮ
በድርጅት ፎጣ ተጠቅልሎ
እቅፍ ድግፍ አርገውት ተሸብልሎ
እንዳይተች:- እንዳይጋለጥ ተማምሎ
ዘረኛን አሸሞንሙኖ ገፁን ኩሎ
እኛም እንላለን!
"እንዲች ናት ፍትህ የነ አያ ጅሎ::”

አንዳንዴማ
የሃሳብ ማዕበል ሲያደርገኝ ሰመም
እንዲያው ለድንገቱ
ተፈልስፎ እንደሆን ልዩ ቅመም
እንደ ኬሚካል አሊ የመሳሰሉቱ
አልኬሚስቱ
በጥበባቸው የሠሩቱ
አድናቆት ያተረፈ በዓለማቱ
"በአንድ ሌሊት እንደተኛ ተለውጦ
ካማራነት የሚቀይር ወደ ወይጦ::
ወይም
ከትግሬነት ወደ አማራ
ከኦሮሞነት ወደ ሱምራ::”
ታዲያ ወዲያ አረጉት ወዲህ

ይለዋወጥ ይሆን የሰው ፍላጎቱ?<br>
እኔማ:-<br>
አንድ ዓይነት ነው እላለሁ በመሠረቱ::<br>
ሁሉም ይፈልጋል እንዲታወቅ ሰውነቱ<br>
እንዲጠበቅ ነፃነቱ የግል መብቱ<br>
ነገር ግን<br>
ዛሬ እንደ እህል የዘሩት በያይነቱ<br>
ያደከመን ዘረኝነቱ<br>
ለማን ሊጠቅም? የት አባቱ!<br>
ጣሉት! አምዘግዝጉት!<br>
ጊዜ አትስጡት!